***የስብሰባው ዓይነት፣ የፓናል ውይይተ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አጀንዳ አድማስ ማስፋት***
***ቀን፡ ነሀሴ 1፣ 2011***
***ቦታ፡ ጌት ፋም ሆቴል***

- የተከበራቹ ፓናሊስቶችና አወያይ
  - ዶ/ር ሲሳይ መንግስቴ፣ ዶ/ር ኮንቴ ሙሳ፣ ዶ/ር መላኩ ተገኘ፣ አቶ ሙሼ ሰሙ፣ አቶ መስፍን ማናዜ፣
- የተከበራቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች፣ የመንግስት እና መንግስታዊ መስሪያ ቤት ተወካዮች፣
- የተለያዩ ሚዲያ ተቋማት ተወካዮች፣
- የተወደዳች የፓነል ውይይቱ ተሳታዎች፣

**ክቡራትና ክቡራን፣**

አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ አሰራር እና ባህል በሀገራችን እውን እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጾ ለማድረግ የተነሳው **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ የቆየውን የፖለቲካ ፍልስፍናና አጀንዳዎች ቆም ብለን እንድናስብ፣ ይዘታቸውን እንድንመረምር፣ ተገቢነታቸውን እንድናጤንና፣ ካለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ጋር መጣጣማቸውን እንድናሰላስል፣ **"የኢትዮጵያን የፖለቲካ አጀንዳ አድማስ ማስፋት"** በሚል ርእስ በተዘጋጀው የፓነል ውይይት ላይ በመገኘታቹሁ የተሰማኝን ከፍተኛ ደስታ በራሴ እና በባልደረቦቹ ስም እገልጻለሁ፡፡

በሀያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ መባቻ ላይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደተጀመረ የሚነገርለት የለውጥ እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩ ግራ ዘመመም በሆነ የማርክሲስት ሌኒንስት ርእዮተ ዓለም ላይ ተመስርቶ የማንነትና የብሄር ጥያቄ የሀገራችን የፖለቲካ ትግል መሰረት እና ዋነኛው መገለጫ ሆኖ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ በወቅቱ የነበሩ የተማሪ እንቅስቃሴ እና የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች በሀገራችን ለረዥም ግዜ የቆዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጭቆናዎችን ሲተነትኑ በግዜው ከነበሩት የፖለቲካ ጥያቄዎች ገዝፎ የማንነት ጥያቄ ተለይቶ ወጣ፡፡ በዚያ ወቅት በማንነት ጥያቄ ዙርያ በርካታ ጽሁፎችና መጣጥፎች የተጻፉ ሲሆን የዋለልኝ መኮንን "On the Question of Nationalities in Ethiopia" በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡

በዚህም ምክንያት የብሄር ጥያቄ የአብዛኛዎቹ የወቅቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ዋነኛው እና ብቸኛው የፖለቲካ ጥያቄ ለመሆን ቻለ፡፡በተለያየ ግዜ ተመስርተው የከሰሙ ወይም እስከ አሁን የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች የብሄር ጥያቄን ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳቸው ማጠንጠኛ አድርገው ተነሱ፡፡ ከንጉሱ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ በደርግ የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት በርካታ የብሄርና ብሄረሰብ ነጻ አውጪ ድርጅቶች በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ተመስርተው አንዳንዶቹ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል፣ ሌሎቹ በትጥቅ ትግል የሀገራችን ፖለቲካ መሰረታዊ ችግር ያሉትን የብሄር ጭቆና ለማስወገድ መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

የዘውዳዊው አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን በተቆጣጠረ ማግስት በሁሉም የሀገራችን ክፍል የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች አብዛኞቹ ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳቸው በማንነት ጥያቄ ላይ የሚያጠነጥን ነበር፡፡ የደርግን አምባገነናዊ ስርአት በትጠቅ ትግል የተዋጉት እና ያሸነፉት ኃላም ግንባር ፈጥረው ሀገሪቱን ላለፉት 28 ዓመታት የመሩት የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶች ሁሉም ራሳቸውን የብሄር ነጻ አውጭ ግንባር አድርገው የተደራጁ ኃይሎች ናቸው፡፡

በተለያየ ደረጃ ብሄር ተኮር ፖለቲካ ከሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ኃይሎች በተቃራኒ የቆሙ እና **"የህብረ-ብሄር"** ወይም **"የዜግነት"** ፖለቲካን እናራምዳለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሙሉ አቅማቸውን የብሄር ፖለቲካን በመቃወም አለፍ ሲልም የብሄር ፖለቲካን አምርረው በማውገዝና እውቅና በመንፈግ በሌላ ጽንፍ ላይ ቆመው **"የህብረ-ብሄር"** ፖለቲካን

ያራምዳሉ፡፡የብሄር እና ህብረብሄር ፖለቲካ አንዱ ለሌላው በስጋትነት እየቀረበ እና ሁለቱም የፖለቲካ ጎራዎች ራሳቸውን ለማጠናከር የሌላውን ችግር በማብራራት የሀገራችን ፖለቲካ ከብሄር ጉዳይ ፈቅ እንዳይል የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል፡፡

የማንነት ፖለቲካ ለአንዳዶቻችን ለሀገራችን ሰላም፣ እኩልነት እና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ወሳኝ ሆኖ ሲቀርብ ሌሎቻችን በማንነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀት የውድቀት፣ የግጭትና የመበተን አደጋ ምንጭ ሆኖ ይታያል፡፡**ሁለቱን የፖለቲካ አስተሳሰቦች ሊያስታርቅ የሚችል ሶስተኛ ወይም መካከለኛ መስመር በብዙዎች ሲቀነቀን አይስተዋልም፡፡** ሲጠቃለል የብሄር እና የማንነት ጥያቄ ባለፉት 60 አመታት የሀገራችን ፖለቲካ ምሰሶና ማገር፣ ጣራና ግድግዳ ሆኖ የቆየ ሲሆን የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና የብሄር ጥያቄ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነዋል፡፡

*በብሄር ላይ ብቻ ያተከረው ፖለቲካችን ከብደት እና ጉዳት*

### ውድ የፕሮግራሙ ታዳሚዎች

የበርካታ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መኖሪያ ለሆነችው ሀገራችን የብሄር ጥያቄ ከዋና ዋና የፖለቲካ ጥያቄዎች አንዱ መሆኑ የማይጠበቅ አይደለም፡፡ በተለይም ማንነትን መሰረት ያደረገ አድሎና ጭቆና በስፋት ተፈጽሟል ተብሎ በብዙዎች በሚታመንባት ሀገር ዜጎች ብሄርን ወይም ቋንቋን መሰረት አድርገው መደራጀታቸው እና መታገላቸው የሚያስገርም አይደለም፡፡ ባለፉት ሶስት አስርተ አመታት የሀገራችን ፖለቲካ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ የብሄር ፖለቲካ ሆኗል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች መነሻ እና መድረሻ ፣ አጀንዳ እና ትርክት፣ የምርጫ ማኔፌስቶ እና ፕሮፓጋንዳ ወዘተ ባብዛኛው ብሄርን፣ ማንነትን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሆኗል፡፡ የማንነት ጥያቄ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባት ሀገራችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሳይቀሩ የብሄር ድባብ ያንዣበበባቸው ሆነዋል፡፡

*የብሄር ፖለቲካ ያስከፈለን ዋጋ*

በሀገራችን የብሄር ጥያቄ ዋነኛው እና ብቸኛው የፖለቲካ አጀንዳ መሆኑ ሀገራችንን እና ህዝባችንን ትልቅ ዋጋ አስከፍሏል፡፡ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የሚከሰቱ ግጭቶች መንስኤያቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከማንነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የተሻለ ነው ተብሎ የሚታመነው የፌዴራል ስርአት ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ተግባራዊ የተደረገበት አግባብ የብሄር ጥያቄ ይበልጥ እንዲጦዝ እና ብሄር-ተኮር ግጭቶች ይበልጥ እንዲባባሱ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ተንቀሳቅሶ መስራት፣ መማር ወይም መኖር አስቸጋሪ ሆኗል፡፡የህዝቦች የአብሮነት እና የወንድማማችነት ስሜት እጅጉን ተቀዛቅዞ የስጋት ድባብ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ነግሷል፡፡ ባለፉው አንድ አመት በሀገራችን የተጀመረው የለውጥ ሂደት የፈጠረው የአስተዳደር ክፍተት ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ከፉኛ እንዲባባሱ አድርጓል፡፡

*የተረሱ አጀንዳዎች*

የማንነት ጥያቄ ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳ በሆነባት ሀገራችን ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ተንሰራፍተዋል፡፡ከአለም እጅግ ድሀ ሀገሮች አንዷ የሆነችው እትዮጵያ ህልውናዋን ጭምር የሚፈታተኑ፤ ዘር፣ ቋንቋ፣ ብሄር፣ ሀይማኖት እና ቀለም ሳይለዩ የሁሉም የሀገራችን ህዝቦች ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች ተደራርበውባታል፡፡ የማንነት ጥያቄ ብቻውን ተለይቶ ይህን ያክል መስፋፋቱ ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ህልውና እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ትኩረት እንዳያገኙ ጋርዶናል፡፡

### ከቡራትና ከቡራን

በሀገራችን አራቱም ማእዘን የሚኖሩ ገበሬዎች፣ አርብቶ አደሮች፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ተማሪዎች ወዘተ መሰረታዊ ችግሮቻቸው ተመሳሳይ ነው-ድህነት፣ በሽታ፣ ርሀብ፣ ስራ አጥነት፡፡ የትምህርት፣ ጤና፣

የንጹህ መጠጥ ውሀ፣ ትራንስፖርት፣ ልብስና መጠለያ፣ በቂ ምግብ፣ ሰላም እና ደህንነት የመላው ሀገራችን ህዝቦች የዘመናት ህልሞች ናቸው፡፡ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎች እና ወላጆች ጥራት ያለው ትምህርት በተመጣጣኝ ዋጋ ይሻሉ፡፡ በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ምርጥ ዘር ማዳበሪያ፣ የግብርና ግብአቶችና ዘመናዊ ሙያ የሚያስገኛቸው ስልጠና ይሻሉ፡፡ ከአመት አመት እየተባባሰ የመጣው የትራንስርት ችግር የዜጎች መሰረታዊ ጥያቄ ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት በቂ የፖሊሲ ውይይት ሲካሄድ አይስተዋልም፡፡ በከተሞች ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት የሚጠብቁ ረዣዥም ሰልፎችን ማየት በጣም የተለመደ ትእይንት ሆኗል፡፡

ልጓም ያጣው የዋጋ ግሽበት እና የኑሮ ውድነት የዜጎችን ህይወት ክፉኛ አመሰቃቅሎታል፡፡ ላለፉት አስርተ አመታት ኢ-ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እና መረን በለቀቀ ሙስና የተበላሸው የሀገራችን ኢኮኖሚ በአንድ በኩል በአለም ተወዳዳሪ ቢሊየነሮችን ሲፈጥር በሌላ በኩል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የድሀ ድሀዎችን ቁጥር ፈጥሯል፡፡ ኢትዮጵያውያን ከሁልም የሀገራችን ክፍሎች፣ ከሁልም ብሄር እና ሀይማኖት ባህር ማዶ ይሰደዳሉ፣ ይሞታሉ፡፡ ሆኖም ችግራቸው ሀገራዊ አጀንዳ ሆኖ ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኝ የሚችል ስራ ሲሰራ እምብዛም አይታይም፡፡ በሀገራችን አራቱም ማእዘን የሚኖሩና ከሀገራችን ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች ዋና ችግራቸው ስራ አጥነት ሲሆን ወጣቶቻችንን ላልተፈለገ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከመዳረግ ባሻገር የህልውና ጉዳይ ለመሆን በቅቷል፡፡

በጠረፋማ እና ቆላማው የሀገራችነ ክፍል የሚኖሩ አርብቶ አደሮች ካሉበት እጅግ አስከፊ የኑሮ ውጣውረድ የሚታደጋቸው የፖሊሲ አማራጮችን በአፋጣኝ የሚሹ ቢሆንም ጉዳዮቸው በሀገራችን ፖለቲከኞች ለአፍታም ሲወሳ አይሰማም፡፡ ከሀገራችን የቆዳ ስፋት 60% የሚሆነው የአርብቶ አደር ማህበረሰባችን የሚኖሩባቸው አካባቢዎች መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የአካባቢ ጥበቃ፣ የደን መመናመን፣ በርሀማናት የመሳሰሉ ዓለም አቀፋዊ አጀንዳወች በሀገራችን ፖለቲካ ብዙም ትኩረት ሲያገኙ አይስተዋልም፡፡

ሁሉም የሀገራችን ህዝቦች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር በሰላም፣ በወንድማማችነት፣ በአንድነት፣ በመቻቻል፣ በፍቅር መኖርን ይሻሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉንም የሀገራችን ህዝች የጋራ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት ፖለቲካዊ ባህል እና ታሪክ የለንም፡፡ በማንነት ፖለቲካ ብቻ ላይ ማተኮራችን ከሌሎች አህጉራዊና ዓለምአቀፍ ይዘት ካላቸው ጉዳዮች እንድንርቅ አድርጎናል፡፡ በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው ሉላዊነት የተነሳ የአፍሪካ እና የዓለም ምጣኔ ሀብትና ግንኙነቶች ይበልጥ እየተቆራኙ እና እየተወሳሰቡ የመጡ ሲሆን በዚህ ፈርጀ ብዙ ዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ውስጥ ጥቅማችንን አስጠብቀን ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችሉ የፖሊሲ አማራጮች ላይ በቂ ትኩረት አላደረግንም፡፡ በአካባቢያዊ እና አህጉራዊ የንግድ፣ የባህል እና ፖለቲካ ትስስር ውስጥ ዜጎች በቂ እውቀትና ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ የፖሊሲ አማራጮች ላይ ፖለቲከኞች ውይይቶች ሲካሄዱ አይታይም፡፡

### ውድ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች

ቀደምት ኢትዮጵያዊያን ሀገራዊ እና አለምዓቀፋዊ ሁኔታዎች ታሳቢ ያደረጉ የፖለቲካ አጀንዳዎች ላይ ታግለው አልፈዋል፡፡ ከ **ያ ትውልድ** የምንወስደውን መልካም የትግል ተሞክሮ ወስዶ ለሀገራችንና ላለንበት ዘመን የሚመጥን አጀንዳ መቅረጽ የዚህ ትውልድ ግዴታ ነው፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ አክቲቪስቶች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች ወዘተ የሀገራችን ፖለቲካ አጀንዳ አድማሱ እንዲሰፋ ትኩረት የተነሳቸው ጉዳዮች በቂ ትኩረት እንዲሰጣቸው ሰፊ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ፓርቲያችን **"የኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ ማስፋት"** በሚል ርእስ ያዘጋጀው የዛሬው የፓነል ውይይት ከዚህ አንጻር መጠነኛ አስተዋጾ ይኖረዋል ብለን እናምናለን፡፡ ባህልን በተለይም የፖለቲካ ባህልን መቀየር ረዥም ግዜ እና ሰፊ ስራ የሚጠይቅም ቢሆንም በአንድ ወቅት ሊጀመር የግድ ነው፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በቀጣይ በተለያዩ

የፖለሲ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩ ልዩ ውይይት መድረኮችን የሚያዘጋጅ ሲሆን **የዛሬው የውይይት መድረክ** በቀጣይ ለምናደርጋቸው ውይይቶች እንደ መነሻ እንዲሆን ታስቦ ነው፡፡

**ውድ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች**

ዛሬ ላይ የምናካሂደው የውይይት መድረክ የሀገራችን ፖለቲካ አልፋ እና ኦሜጋ የሆነው የማንነት ፖለቲካ አድማስ እንዲሰፋ እና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል መሰረት የሆኑ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጣቸው ማስቻል ነው፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ተመሳሳይ መድረኮችን ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያዘጋጃል፡፡

በመጨረሻም በዛሬው የውይይት መድረክ ላይ ተገኝተው ሀሳብና እውቀታቸውን ለማጋራት ፈቃደኛ ለሆኑ ውድ ተናጋሪዎች፣ ለፕሮግራሙ መሳካት በገንዘብና በቴክኒክ ድጋፍ ላደረጉ **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም አጋሮቻችን ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ የፓነል ውይይቱ የተሳካ እንዲሆን እመኛለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ**